Randy I. Dorn Old Capitol Building · PO BOX 47200 · Olympia, WA 98504-7200 · http://www.k12.wa.us

## የ Washington English Language Proficiency Assessment (የዋሽንግተን እንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት መገምገሚያ) ምንድነው?

የWashington English Language Proficiency Assessment (WELPA) ተማሪዎች በአውራጃው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማጎልበቻ ፕሮግራም (ELD) በኩል ድጋፍ ያስፈልጋቸው እንደሆነ መገምገሚያ ፈተና ነው። ይህ ግምገማ የእንግሊዝኛ ቋንቋን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የማዳመጥና የመናገር እውቀትና ችሎታ የሚፈትን ነው። ከመዋለ ሕጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ይህንን ፈተና በዓመት አንድ ጊዜ ወስደው በትምህርት ቤት ውስጥ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሲማሩ ምን ያህል እንዳሻሻሉ ለመመዘን ይጠቅማል። በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን እንግሊዝኛ ቋንቋን ማወቅና መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋን ለመማር ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተገቢውን እርዳታ ማግኘታቸው አስፈላጊ ነው።

## ተማሪዎች ለአውራጃው ትምህርት ቤቶች (ዲስትሪክት) የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት ፕሮግራም ብቁ የሚሆኑት እንዴት ነው?

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሲመዘገቡ፣ ለወላጆች “ልጅዎ ከእንግሊዘኛ ሌላ ቋንቋ በመጀመሪያ ይናገር/ትናገር ነበር?” የሚል ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። መልሱ “አዎ” የሚል ከሆነ፣ ተማሪው/ዋ የዋሽንግተን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ግምገማ (WELPA) የምደባ ፈተና ይፈተናል/ትፈተናለች። በምደባ ፈተናው ደረጃ 1 (የጀማሪ)፣ 2 (መሐከለኛ)፣ ወይም 3 (ከፍተኛ) ውጤት የሚያገኙ ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋቸውን እንዲያሻሽሉ ለተጨማሪ ድጋፍ ብቁ ይሆናሉ።

## በአውራጃው ትምህርት ቤቶች (ዲስትሪክት) የእንግሊዘኛ ቋንቋ ዕድገት ፕሮግራም በኩል ተማሪዎች ለምን ያህል ጊዜ አገልግሎቶችን ያገኛሉ?

ተማሪዎች እንግሊዘኛ ለመማር ድጋፍ እስከሚያስፈልጋቸው የጊዜ መጠን ድረስ በፕሮግራሙ ውስጥ ይቀጥላሉ። የተማሪዎችን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታና የንባብ፣ የጽሑፍ፣ የማዳመጥ፣ እና የመናገር ችሎታዎች እድገትን ለመመዘን የ WELPA ፈተና ይሰጣል። የ WELPA ፈተና የደረጃ 1፣ 2፣ ወይም 3 ውጤት ተማሪው/ዋ በፕሮግራሙ መቀጠል ያለበት/ባት መሆኑን ይወስናል። ተማሪዎች የ WELPA የማለፊያ ነጥቦችን ሲያሟሉ በአጥጋቢ ሁኔታ ከፕሮግራሙ ይዛወራሉ።